የመጽሐፍ ቅዱስ ጥናት ትምህርት መማርያ ኖት

መግቢያ

የጽሑፍን ጥበብ ለሰው ልጆች የገለጠው እግዚአብሄር በሄኖስ ዘመን የፊደላትን መልክ በሰማይ ሰሌዳ ላይ በማሳየት ነው። ዘፍ 4:–26

ምንም ፊደላት በሄኖስ ዘመን ቢታዩም በሀሊና የሚመላለስ ሀሳብን በመጽሐፍ መግፍ የተጀመረው 7 ተኛ ትውልድ በሆነው በቅዱስ ሄኖክ ነው።

የመጻህፍት አይነት

ቤተ ክርስቲያናችን በአለም ውስጥ የሚገኙትን መጻህፍት ለ 3 ት ከፍላ ታያቸዋለች።

፩. ቅዱሳት(አምላካውያን) መጻህፍት

- እነዚህ መጻህፍት ቅዱስ እግዚአብሄር በየዘመኑ ቅዱሳንን እያስነሳ ለሰው ልጆች ህይወት መመሪያ ይሆን ዘንድ በመንፈስ ቅዱስ ገላጭነት ያፃፋቸው መጻህፍት ናቸው። እነዚህም አሥራው(ስሮች) እና አዋልድ(ልጆች) በማለት ለሁለት ይከፈላሉ።

፪. ምኑናት(አለማውያን) መጻህፍት

- እነዚኛዎቹ ደግሞ መንፈሳዊ ህይወታችንን የማይነዱ ነገር ግን ለመንፈሳዊ ህይወታችን የማይጠቅሙ ናቸው። ምሳሌ፡— ልብ ወለድ ፣ የታሪክ መጻህፍት ፣ የአለማዊ ትምህርት መማሪያ መጻህፍት ወዘተ...

፫. ርኩሳት መጻህፍት

- ርኩሳት የምንላቸው ደግሞ የቅዱሳት መጻህፍት ተቃራኒዎች ናቸው። ክህደትን ፣ ጎጥያትን እና ኑፋቄን የሚያስተምሩ የያዙ መጻህፍት ናቸው። የሐዋርያት ሥራ 19፡—19 ምሳሌ:—ጥንቆላ ፣ ኮከብ ቆጠራ ፣ የኑፋቄ መጻህፍት ወዘተ...

1) የመጽሐፍ ቅዱስ የቃሉ ትርጉም

መጽሐፍ ቅዱስ "መጽሐፍ" እና "ቅዱስ" ከሚሉ ሁለት ቃላት የተገኘ ነው።

—መጽሐፍ ማለት የልዩ ልዩ ጽሁፎች ጥራዝ ማለት ነው።

—ቅዱስ ማለት የተለየ ፣ ንጹህ ፣ ክቡር ፣ የተመረጠ ማለት ነው።

* መጽሐፍ ቅዱስ ማለት በአንድ ጥራዝ ሥር የተሰባሰቡ የተለዩ ፣ የተከበሩ ፣ የተመረጡ ፅሁፎች ማለት ነው።

2) ለምን ቅዱስ ተባለ?

✔ አስገኚው የቅድስና ምንጭ ቅዱስ እግዚአብሄር ስለሆነ ዘሌ 19፡—2 ፣ 1ኛ ጴጥ 1፡—15–16

✔ ጸሀፊዎቹ ከእግዚአብሄር የተላኩ በመንፈስ ቅዱስ የተመሩ ቅዱሳን ናቸውና ራዕ 1፡—11 ፣ ኤር 30፡—2

✔ አንባቢ ፣ ሰሚዎች እና ፈፃሚዎችን ለቅድስና ስለሚያበቃ ራዕ 22፡—7

✔ ዘመን የማይሽረው በመሆኑ(4014 ቅ·ል·ክ—አሁን)

✔ የስርዓት ምንጭ ስለሆነ

✔ ስለ አለፈው ፣ አሁን ስላለው እና ስለወደፊቱ በርግጥ ስለሚናገር « ድንግል በድንግልና ፀንሳ በድንግልና ትወልዳለች።»

✔ በመጽሐፍ ቅዱስ የተፃፉ ታሪኮች እውነት መሆናቸውን የሚያሳዩ ሳይንሳዊ ግኝቶች መገኘታቸው

ምሳሌ · የአዳም እና ሄዋን ታሪክ · የጥፋት ውሀ(ኖህ) ታሪክ

3) መጽሐፍ ቅዱስ በማን ፣ መቼ ፣ የት እና እንዴት ተፃፈ?

3·1 መጽሐፍ ቅዱስ በማን ተፃፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ ከተለያየ የስራ ዘርፍ በተጠሩ ከ 40 በላይ ቅዱሳን ተፅፏል።

ለምሳሌ፦— ሠለሞን ከንጉስነት ፣ ሕዝቅኤል ከካህንነት ፣ ማቴዎስ ከቀራጭነት ፣ ሉቃስ ከህክምና ወዘተ...

3·2 መጽሐፍ ቅዱስ መቼ ተፃፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፈ ሄኖክ ከተፃፈበት 4014 ቅ/ል/ክ ራዕይ ዮሐንስ እስከተፃፈበት 99 ዓ·ም ድረስ ተፅፏል።ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለመፃፍ ከ 4100 ዓመታት በላይ ወስዶበታል።

ስለዚህ የመጀመሪያው መጽሐፍ (መጽሐፈ ሄኖክ) ከተፃፈበት እስከ አሁን ድረስ 6027 ዓመታትን በማስቆጠር የአለማችን ቀደምት መጽሐፍ ያደርገዋል።

3·3 መጽሐፍ ቅዱስ የት ተፃፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ ቅዱሳን በተለያየ ጊዜ እንደተፃፈ ሁሉ በተለያየ ቦታም ተፅፏል።

አሁን ካለው መልክዐ ምድራዊ አቀማመጥ አንፃር አፍሪካ ፣ እስያ እና አውሮፓን ያጠቃልላል።

✔ አብዛኛዎቹ የብሉይ ኪዳን መጻህፍት በእስራኤል ፍልስጤም ተፅፈዋል።

✔ አብዛኛዎቹ የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት በእስያ ተፅፈዋል።

* በተለየ ቦታ የተፃፉ የብሉይ እና የሀዲስ ኪዳን መጻህፍት

መጻህፍት	የተፃፈበት ቦታ
የኦሪት መጻህፍት	በሲና ምድረበዳ(ሳውዲ)
መጽሐፈ አስቴር	በፋርስ(ኢራን)
ትንቢተ ዳንኤል	በባቢሎን
ማርቆስ ወንጌል	በግብፅ
መልዕክታት	በሮም እና ግሪክ
ራዕይ ዮሐንስ	በፍጥሞ ደሴት

3·4 መጽሐፍ ቅዱስ እንዴት ተፃፈ?

መጽሐፍ ቅዱስ በተለያዩ መንገዶች ተፅፏል።

✔ በእግዚአብሄር ፈቃድ እና ትዕዛዝ ተፅፏል። ዘጸ 17፥—14

✔ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት ተፅፏል። 2ኛ ጴጥ 1፥—21

✔ በእግዚአብሄር መገለጥ ማለትም ለቅዱሳን በራዕይ በህልም እና ፊትለፊት እየተገለጠ ያፅፋቸው ነበር። ዘኁ 12፥—6–8 ፣ 2ኛ ሳሙ 23፥—2

✔ ከእውነተኛ ምስክሮች ሉቃ 1፥—1–4

✔ ቅዱሳን በየራሳቸው የአፃፃፍ መንገድ እና ባህላቸውን ጠብቀው ጽፈውታል።

✔ በብራና እና በክርስታስ ሰሌዳነት በላባና ቀርከሀ ብዕርነት ከእፅዋት እና እንስሳት ተዋፅዖ ቀለማት መጽሐፍ ቅዱስ ተፅፏል።

4) የመ ጽሐፍ ቅዱስ አለማ (ማዕከላዊ መ ልዕክት) እና ጥቅም

4·1 የመጽሐፍ ቅዱስ አለማ(ማዕከላዊ መልዕክት)

✔ የስነ ፍጥረት አስገኚው እግዚአብሄር መሆኑን ማሳወቅ

✔ መንፈሳዊ(የህይወት) ዕውቀት እና የመዳን ጥበብ መስጠት

✔ ስለህይወት ምንነት እና ስለወደፊቱ ተስፋችን በግልፅ መንገር

✔ የጌታችን ሰው መሆን እንደ እንግዳ ደራሽ አለመሆኑን ይልቁኑም በእግዚአብሄር መለኮታዊ አቅድ አስቀድሞ የተዘጋጀ መሆኑን ማሳየት

4·2 የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅም

✔ የትምህርተ ሀይማኖት መሠረት ነው።

✔ የመልካም ምግባር ምንጭና መመሪያ ነው።

✔ ሰው ከመጽሐፍ ቅዱስ ጥበብ ስጋዊን ይማራል።

ምሳሌ፡— ዘፍ 6፥—14–16:– ለኖህ የመርከብ አሰራርን እንዳስተማረው

ዘፍ 3፥—17:– መሬትን ስለማረስ

2 ኛ ዜና 3፥—3–4:– ስለ ቤተ መቅደስ አሠራር

ዘጸ 32፥—32:– ስለህዝብ አስተዳደር

ኩፋ 19፥—7:–ስለ መድሀኒት አሠራር

✔ መጽሐፍ ቅዱስ ለመቀደስ ፣ ክፋና በጎን ለይቶ ለማወቅ ፣ ማስተዋልን ለማግኘት ወዘተ...ይጠቅማል።

★ **በመጽሐፍ ቅዱስ መፃፍ ውስጥ የእግዚአብሄር እና የቅዱሳን ድርሻ**

*** የእግዚአብሄር ድርሻ**

- እውነትን መግለጥ
- ለመፃፍ ማነሳሳት
- ከተገለጠላቸው አንዳይወጡ መጠበቅ

*** የቅዱሳን ድርሻ**

- የህይወታቸው ቅድስና
- እግዚአብሄር የሚገልጠውን ከሰው ባህልና ባህሪ ጋር ማገናዘብ
- መጻፍ

5)የመጽሐፍቅዱስዝግጅት

5·1 የመጽሐፍ ቅዱስ መሠባሰብ

★ ከዚህ ቀደም ለማየት እንደሞከርነው መጽሐፍ ቅዱስ በተለያየ ጊዜና ቦታ ተፅፏል። ከ 2 ተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ጀምሮ ግን መጻሕፍትን ማሰባሰብ ተጀምሯል።

★ መጽሐፍ ቅዱስን ያሰባሰበው ራሱ መንፈስ ቅዱስ ነው። ኢሳ 34፥—16

★ ማሥራውያን እና ሰብአ ሊቃናት ለትርጉም ብሉያትን አሰባስበዋል።

★ የእስክንድርያው ኮዴክስ በ 822 በብራና ቅጠል ሙሉ ብሉይና ሐዲስ ኪዳንን(የቀሌሜንጦስ መጽሐፍን ጨምሮ) ያሰባሰበ ነው።

የመሠብሠባቸው ምክንያት

✓ የመናፍቃን መነሳት

✓ የቤተ ክርስቲያን የትርጓሜ ት/ቤት መስፋፋት ምክንያት ለምሳሌ የአንጾክያና የግብፅ እንዲሁም የየመን

✓ የሰማዕታት መነሣት እና የትኞቹን እናድን የሚል ጥያቄ

5·2 የመጽሐፍ ቅዱስ መዘጋጀት

★ መጽሐፍ ቅዱስ አሁን ያለበት ደረጃ ላይ ለመድረስ የተለያዩ ደረጃዎችን አልፏል።

★ ብሉያት የተፃፉበትን ዕብራይስጥ አናባቢ እና የቋንቋ ምልክት በመጨመር ለንባብና ትርጉም ያመቻቹት ማሥራውያን ናቸው።

★ አሞንዮስ እና አውሳብዮስ መጽሐፍ ቅዱስን በክፍል ከፋፍለው አዘጋጅተዋል።

★ በ 1228 ዓ·ም ስቲፋን ላንግቶን በምዕራፍ ሲያዘጋጀው በ 1551 ዓ·ም በሮበርት እስቲን (ስቲፋነስ) በቁጥር ተከፋፍሏል።

★ በመጨረሻም በ 16 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የመጽሐፍ ቅዱስ ጎዳግ ተዘጋጅቷል።

5·3 የመጽሐፍ ቅዱስ አሰያየም

- ለቅዱሳት መጻሕፍት ስያሜ የሠጡ ራሳቸው ጸሐፍያኑ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ግን በኋላ በተነሱ አበው አማካኝነት በጸሐፊው በይዘታቸው እና በመግቢያቸው መሠረት መሰየማቸውን እናገኛለን።

ሀ) በጸሐፊው ስም የሚጠሩ፡— መጽሐፈ ኢያሱ ፣ መጽሐፈ ሄኖክ... ወዘተ

ለ) ከይዘታቸው(መጽሐፉ ከሚይዘው ሀሳብ) ፡— ኦሪት ዘፍጥረት ፣ መጽሐፈ ኩፋሌ ፣ መጽሐፈ ነገስት

ሐ) በጸሐፊውና በይዘታቸው የሚጠሩ፥— *መጎልየ መጎልየ ዘሰሎሞን ፣ ትንቢተ ኢሳይያስ*

መ) በሀገር(ከተማ) ስም የሚጠሩ፥—የቅዱስ ጳውሎስ መልእክት ወደ ሮሜ ሰዎች ፣ ወደ ቆሮንቶስ ሰዎች

ሠ) በተላኩላቸው ሰዎች ስም የሚጠሩ፥— 1 ኛ እና 2 ኛ ጢሞቴዎስ ፣ ፊልሞና ፣ ቲቶ

ቁልፍ ቃላት

- **ማሠራውያን፥—** በዕብራይስጥ ባህል ማለት ነው። ከ 200 ቅ/ል/ክ እስከ 8 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበሩ እና የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ያሰባሰቡ የገለበጡ ያዘጋጁና ቀኖና የሠሩ የአይሁድ ሊቃውንትን ያመለክታል።
- **ሰብአ ሊቃናት፥—** እስክንድርያ የነበሩየ አይሁድ በጠየቁት መሰረት ከ 285–246 ቅ/ል/ክ የነበረው የግሪክ ንጉስ በጥሊሞስ ፊላዲልፎስ 2 ኛ ትዕዛዝ ብሉያትን ከዕብራይስጥ ወደ ግሪክ የተረጎሙ አይሁድ ሊቃናት ናቸው።
- **ኮይክስ፥—** የላቲን ቃል ሲሆን በጥንት ዘመን በፓፒረስና በብራና ተጽፈው ለዘመናችን የደረሱየደረሱ ጽሑፎች ናቸው።

6) ቀኖና መጻሕፍት

* ቀኖና መጻሕፍት ሲባል በቤተ ክርስቲያን የተወሰኑትን እና ተቀባይነት ያላቸውን መጻሕፍት ቁጥርና ዝርዝር የሚያመለክት ነው።

ቀኖና መጻሕፍት ለምን አስፈለገ?

* ለመለየት እውነተኞቹን ቅዱሳት መጻሕፍት ከሐራጥቃ(መናፍቃን) አስመሳይ መጻሕፍት ለመለየት በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት መነበብ የሚገባቸውን መወሰን አስፈላጊ ሆኖ ስለተገኘ ቀኖና መጻሕፍት ተዘጋጅቷል።

ቀኖና መጻሕፍት መመዘኛዎች

- ጸሐፊዎቹ ቅድስናቸው የተመሰከረ መሆን አለበት
- ይዘቱ ከቤተ ክርስቲያን መሠረት ጋር መጋጨት(መውጣት) የለበትም
- በቤተ ክርስቲያን የተመሰከረለት መሆን አለበት

የቀኖና መጻሕፍት ጥቅም

- ✓ ልዩ ልዩ የኑፋቄ ትምህርቶች እንዳይሰገሰጉ
- ✓ ከአላውያን ነገስታት ጥፋት በዋሻ ፣ በፍርክታ ፣ በልጆቿ ልቦና በማሳደር አቆይታ ከትውልድ ወደትውልድ ለማስተላለፍ
- ✓ ሐሰተኞችን ከእውነተኞቹ ለይቶ ማረጋገጫ ለመስጠት

6·1 የብሉይ ኪዳን ቀኖና

* በዓለም ላይ ለብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ሁለት መነሻዎች አሉ።

1· የዕብራይስጥ፥— እነዚህ በሦስት ደረጃዎች ተቀንሰዋል(ተቀባይነት አግኝተዋል።)

ሀ) ቶራ/ኦሪት፥— አይሁድ አምስቱ ብሄረ ኦሪትን ከባቢሎን ምረኮ በኋላ በቀኖና ተቀብለዋል።

ለ) ነቢያት፥— በ 3 ኛ መቶ ክፍለ ዘመን ቅ/ል/ክ የነብያት መጻሕፍት ትንቢት በአይሁድ ሊቃናት ታምኖበት በቀኖና ተቆጥሯል።(ኢያሱ ፣ መሳፍንት ፣ ሩት ፣ ኢሳይያስ ፣ ኤርምያስ ፣ ሕዝቅኤል ፣ መጽሐፈ ነገስት ፣ ሳሙኤል 2 ፣ ድጎረት 13) ድጎረት 13 የተባሉት በቤተክርስያናችን መጽሐፍ ቅዱስ ላይ ከዳንኤል እስከ ሚልክያስ የሚገኙትን መጻሕፍት ነው።

ሐ) ጽሑፋት፥— ከመጽሐፈ ዜና መዋዕል እስከ መዝሙረ ዳዊት ያሉትን 11 መጻሕፍት ጨምረው በምድረ ፍልስጤም የቀሩ ረበናት በ 90 ቅ/ል/ክ ኒያሚን በተባለ ቦታ የመጨረሻውን የብሉያት ቀኖና ወስነዋል።

✔ የዕብራውያን መጻሕፍት አቆጣጠር ቅደም ተከተል ግሪኩንና ግዕዙን የማይከተል ሲሆን ክርስቶስ ያልተቀበሉ አይሁድ እና ፕሮቴስታንቶች ከሉተር ጀምሮ ይቀበሉታል።

2· ኦሪት ሊቃናት**(**የሰባው ሊቃውንት ትርጉም**)**፥— 24 ቱን የዕብራይስጥ እና እንደ መጽሐፈ አስቴር ፣ መጽሐፈ ዮዲት እና የመሳሰሉት በመጨመር 46 መጻህፍትን አስቀምጠዋል።

* የሰባው ሊቃውንት እውቅና መሰረት በማድረግ ካቶሊካውያን እና ኦርቶዶክሳውያን በተለይም የኢ/ኦ/ተ/ቤ/ክ ሙሉውን ይቀበሉታል።

6·2 የሐዲስ ኪዳን ቀኖና

* የሐዲስ ኪዳን ቀኖና ከመዘጋጀቱ በፊት ምንጫቸው ያልተረጋገጠ እና በሐራጥቃ(መናፍቃን) አማካኝነት በሐዲስ ኪዳን ጸሐፊያን እና ሌሎች ቅዱሳን ስም የተፃፉ መጻሕፍት ነበሩ።(ከ 50 በላይ ወንጌላት ተፅፈዋል።) ስለዚህ ቀኖና ሐዲስ ኪዳን ማዘጋጀት አስፈልጓል።

* ቤተ ክርስቲያናችን የሐዲስ ኪዳን ቀኖና ስታዘጋጅ ቀኖናተ ሲኖዶሳት እና ቀኖናተ አበው መሰረት በማድረግ ነው።

ተ/ቁ	ቀኖናት	የብሉይኪዳን ቁጥር	የሐዲስኪዳን ቁጥር	ድምር
ሲኖዶሳውያን ቀኖናት				
1	85 ሐዋርያውያት ቀኖናት	42	36	78
2	ቀኖናተ ዘላኦዶቅያ	41	26	67
3	ቀኖናተ ዘቅርጣግና	43	27	70
ቀኖናተ አበው				
4	መልዕክተ አትናቴዎስ	45	29	74
5	ቀኖና ጎርጎርዮስ	37	26	63
6	ቀኖና አምፊሎክዮስ	28	27	65

ማብራርያ

1· በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ሐዋርያት በሲኖዶስ የወሰኗቸው 85 ቀኖናት

2. 60 ኛው የሎዶቅያ ሲኖዶስ ቀኖና

3. በ 419 የተደረገው የቅርጣግና ሲኖዶስ ቀኖና

4. ታላቁ አትናቴዎስ በ 367 በፋሲካ 39 ኛ መልዕክቱ የዘረዘራቸው ቅዱሳት መጻሕፍት

5. ነባቤ መለኮት ጎርጎርዮስ ዘንዚናዙ በግጥም ቅርጽ የዘረዘራቸው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር

6. የኢቆንዮን ሊቀ ጳጳሳት የነበረው አምፊሎክዮስ ስለ ቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር በ 59 ስንኞች ያስተላለፈበት ነው።(691)

የ 81 ዱ ቅዱሳት መጻሕፍት ቀኖና በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን

ሀ) በፍትሐ ነገስት አንቀጽ 2 የቅዱሳት መጻሕፍት ዝርዝር 81 እንደሆነ ይናገራል። መጽሐፉም 81 ብሎ ተነስቶ ሲዘረዝር 73 መጽሐፍትን ይቆጥራል። መተርጉማኑም 8 የሐዲስ ኪዳን የሥርዓት መጻሕፍትን በመጨመር ቁጥሩን አሟልተው ይተረጉማሉ።

ለ) ሊቃዉንት ጉባኤው በ 07/06/1986 ዓ.ም ቃለ ጉባኤ ተቀርጾ ባደረገው የስብሰባ ውሳኔ እንደ መተርጉማኑ 46 የብሉይ 27 የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን ተቀብሎ ስምንቱን የሥርዓት መጻሕፍትን ዘርዝሮ በመጨመር 81 መሆናቸውን አሳውቋል።

የሌሎች ቤተ እምነት አቆጣጠር ወይም ቀኖና

1.አይሁድ በ 90 ዓ.ም በጀሚና ጉባኤ 39 የብሉይ ኪዳን መጻሕፍትን ተቀብለዋል። ምክንያታቸዉም ስለ ክርስቶስ በግልጽ የሚናገሩትን ላለመቀበል እና ለፀረ ግሪካዊ የማንነት አቋማቸው በግሪክኛ የተጻፉትን አለመቀበል ነበሩ።

2. ካቶሊክ አስቀድሞ በቅርጣግና የተጠቀሱትን 70 መጻሕፍትን ብቻ ብትቀበልም ኋላ ግን በ 1546 ዓ.ም በጣሊያኗ ትሬንት ቀኖና መጻሕፍትን ያሳወቀችው ካቶሊክ 46 ብሉይ እና 27 ሐዲስ ኪዳን መጻሕፍትን መቀበሏን አሳውቃለች።

3. ፕሮቴስታንት ሉተር ከካቶሊካዉያን ጋር በተጋባው እልህ በ 1534 ዓ.ም መጽሐፍ ቅዱስን ሲተረጉም 39 ብሉያትን በአይሁድ አቆጣጠር በመመሥረት 27 ሐዲሳትን በመጨመር 66 መጻሕፍትን ብቻ ተቀብሏል።

4. የግሪክ ኦርቶዶክስ 77 መጻሕፍትን 1954 ዓ.ም ባሳተሙት መጽሐፍ ቅዱስ 77 ቱን መጻሕፍትን በመዘርዘር አሳውቀዋልዠ።

7) የመጽሐፍ ቅዱስ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎም

* አብዛኛው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ የተጻፈው በዕብራይስጥ ሲሆን የሐዲስ ኪዳን ደሞ በዕርዕ(ግሪክ) ቋንቋ ተፅፏል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስን በመላው ዓለም ለማዳረስ ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎም አስፈልጓል።

7.1 መጽሐፍ ቅዱስን ከቋንቋ ወደ ቋንቋ መተርጎምያ መንገዶች

1) ቀጥተኛ(**literal**):-ከተጻፈበት ወይም ከአቀባዩ ቋንቋ ቃል በቃል መተርጎም ሲሆን ከተነባቢነት እና የቋንቋ ውበት ይልቅ ቃል በቃል መተርጎምን ይከተላል።

2) ገለጭ(**Discrptive**):-ከቃላት ይልቅ ድርጊት እና ሐሳብን በመግለፅ ተነባቢነት ላይ ያተኩራል።

7.2 የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በዓለም

- በ900 ቅ.ል.ክ በቀዳማዊ ምንሊክ አማካኝነት ወደ ኢትዮጵያ የመጡ የአይሁድ ሊቃዉንት ለመጀመሪያ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ከዕብራይስጥ ወደ ግዕዝ ተርጉመውታል።
- በተለያየ ጊዜ ወደ ግብፅ የተሰደዱ የእስክንድርያ አይሁድ ባደረጉት ግፊት በበጥሊሞስ ሁለተኛ ፒላደልፍስ ትዕዛዝ በ250 ቅ.ል.ክ ሰባሊቃናት የዕብራይስጡን ብሉይ ኪዳን ወደ ግሪክ ተርጉመዋል።
- በሮማንያም ቅዱስ ሚስሮጥና ቅዱስ ሳህክ (3-4 መ/ክ/ዘ) መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አርመንያ ቋንቋ ተርጉመዋል።
- ጀሮም የተባለ አባት በ383 ዓ.ም ወደ ቩልጌት(በሮም የሚኖሩ ቩልገስ የተባሉ ህዝቦች ቋንቋ) ተርጉሞታል።

* እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ መጽሐፍ ቅዱስ የተተረጎመባቸው ቋንቋዎች ላቲን ፣ ቅብጥ ፣ ግዕዝ ፣ ሱርስት ፣ አርሜንያ ፣ ጆርጅያ እና ጎት ናቸው።እነዚህ ከጥንቱ ዕብራይስጥና ግሪክ ቋንቋዎች ትርጉሞች ለሚነሱ ስህተቶች ማረሚያ ስለሆኑ በጣም አስፈላጊ እንደሆኑ ይታመናል።

* ከዚህ በኋላም መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ተለያዩ ቋንቋዎች ተተርጉሟል። በ1443 ዓ.ም የሕትመት መሳርያ መፈልሰፉ የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉምን አበረታቷል።

- በማርቲን ሉተር በ1545 ?ወደ ጀርመንኛ ተተርጉሟል።
- 13-15 መ/ክ/ዘ መጽሐፍ ቅዱስ በሙሉና ልዩ ልዩ ክፍሎች ወደ አብዛኞቹ የአውሮፓ ቋንቋዎች ተመልሰዋል።
- በተለያየ ጊዜም የወጡ የተለያዩ የእንግሊዘኛ ቋንቋ ትርጉሞች አሉ ለአብነትም በንጉስ ጀምስ መልካም ፈቃድ በ1611 ወደ እንግሊዘኛ ተተርጉሟል ይህ የንጉስ ጀምስ ትርጉም ይባላል።
- ከኢትዮጵያና ግብፅ ውጪ በሆኑ የአፍሪካ ሀገራት መጽሐፍ ቅዱስ ወደ ቋንቋቸው የተመለሰው በ19 ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ነው።

* በምድራችን በብዙ ቋንቋዎች ለብዙ ዘመናት በመተርጎም አቻ የሌለው መጽሐፍ ቅዱስ ከ2300 ቋንቋዎች በላይ ለ3000 ዓመታት የተተረጎመ ለአብዛኛው(98 በመቶ) የዓለም ሕዝብ የተዳረሰ መጽሐፍ ነው።

7.3 የመጽሐፍ ቅዱስ ትርጉም በኢትዮጵያ

* ከቀዳማዊ ምኒሊክ ጋር በመጡ ሌዋውያን አማካኝነት ከንጉስ ሰሎሞን የተጻፉ የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በ900 ቅ.ል.ክ አከባቢ ተተርጉመዋል።

* ከቀዳማዊ ምንሊክ በኋላም የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት በተለያየ መንገድ ገብተዋል።

- ✓ ኢየሩሳሌም ለመሳለምና ለንግድ በሄዱ አበው ለምሳሌ ጃንደረባው ባኮስ የሐዋ ሥራ 8:-26
- ✓ ከምድረ ከነዓን በተሰደዱ አይሁድ በነገሥታት መፃፍ
- ✓ ከባቢሎን ምርኮ ምርኮ በኋላ ቅዱሳት መጻሕፍት እንደተለዋወጡ

* ከክርስትና መግባት በኋላ የመጀመሪያው የኢትዮጵያ ጳጳስ ፍሬምናጦስ በ4 ኛ መ/ክ/ዘ ቅዱሳት መጻሕፍትን ከሱርስት ፣ ከዕብራይስጥና ከጽርዕ ቋንቋ ወደ ግእዝ መልሰዋል።

* በ5 ኛ መ/ክ/ዘ ከሶርያና ከታናሿ እስያ ተሰደው የመጡ ዘጠኙ ቅዱሳን መነኮሳት አያሌ መጻሕፍትን ከሱርስትና ከጽርዕ ቋንቋ ወደ ግእዝ መልሰዋል፤ እንዲሁም የ70 ው ሊቃውንት መጽሐፍ ይዘው መተዋል።

* በ14 ኛው መ/ክ/ዘ አባ ሰላማ ካልዕ ሐዲስ ኪዳንን ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ ተርጉመዋል።

* አባ አብርሀም(አባ ሮሜ) በ1816 አራቱን ወንጌላት ፣ በ1821 ሐዲስ ኪዳንን ፣ በ1832 ደሞ ሙሉ መጽሐፍ ቅዱስን ወደ አማርኛ መልሰዋል።

*በ 1832 በታተመው የአባ አብርሀም ትርጓሜ ላይ ማሻሻያ ተደርጎ እና ቤተ ክርስቲያን የምትቀበላቸው የብሉይ ኪዳን መጻሕፍት ተካተውበት በ 1947 ዓ.ም ተሠራጨ በ 1980 ዓ.ም ከመጽሐፍ ቅዱስ ማህበር ጋር በመተባበር የ 1947 እትም እንደገና ታትሟል።

* 27 ቱን የሐዲስ ኪዳን መጻሕፍት በግእዝና በአማርኛ በ 1975 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያናችን አሳትማለች።

* በመጨረሻም በ 1986 ዓ.ም በተቋቋመው የቅዱሳት መጻሕፍት ዝግጅት ጉባኤ አማካኝነት በ 2000 ዓ.ም ቤተ ክርስቲያናችን 46 ቱ ብሉያትን እና 27 ቱ የሐዲስ መጻሕፍትን በአማርኛ አሳትማለች።

* በአሁኑ ወቅት መጽሐፍ ቅዱስ ከ 30 በላይ በሆኑ የሀገራችን ቋንቋዎች ተተርጉሟል።

ትርጉሞች ለምን ተለያዩ?

- ❖ የተጠቀሙት የትርጉም መንገድ
- ❖ የዶግማ ልዩነት
- ❖ ከተለያዩ ምንጮች በመተርጎማቸው
- ❖ በተለያዩ አካላት እና ሃይማኖታዊ እውቀት በሌላቸው ሰዎች በመተርጎሙ

የትርጉሞች መብዛት የሚያስከትለው ችግር

1. አንባብያንን ያደናግራል
2. አንባብያን እውነተኛነቱን እንዲጠራጠሩ ያደርጋል
3. መሠረታዊ የነገረ ሀይማኖት ልዩነት ያመጣል

ትክክለኛውን ለመለየት ምን እናድርግ?

- ✓ የተለያዩ ትርጉሞችን ማነፃፀር እና ሌሎች ጥቅሶች ጋር ማመሳከር
- ✓ ሙሉ ሐሳቡን ማንበብ
- ✓ የቤተ ክርስቲያንን ፈለግ መከተል